# መሸጋገሪያ ድጋፍ ምትክ ክፍያ ፈቃድ መስጫ
## Interim Assistance Reimbursement Authorization

| የደንበኛው ስም | የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር | የደንበኛው ቁጥር፥ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| የነዋሪ አድራሻ | ከተማ | ስቴት | ዚፕ ኮድ |
| የፖስታ መላኪያ አድራሻ | ከተማ | ስቴት | ዚፕ ኮድ |

**ስቴት የሚለው ቃል የዋሽንግተን ስቴት የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች መምሪያ ማለት ነው። እኔ፣ ለእኔ እና የእኔ የሚሉት ቃላት ስሙ ከላይ የተጠቀሰው ደንበኛ ማለት ናቸው። SSA የሚለው ቃል የማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር (Social Security Administration) ማለት ነው። SSI የሚለው ቃል የማህበራዊ ዋስትና ድጋፍ ሰጪ የዋስትና ገቢ (Social Security Supplemental Security Income) ማለት ሲሆን የፌደራል የገቢ ድጋፍ ሰጪ ፕሮግራም ነው። መሸጋገሪያ ድጋፍ (Interim Assistance) የሚለው ቃል በስቴት ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የሚሸፈኑ የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ሆነው በስቴቱ ለ ወይም ስለ ደንበኛው የደንበኛውን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚከፈሉ ኋላ ላይ በፊርማ ወይም በ SSI ክፍያ ላይ እንደገና የሚጸፍ ማለት ነው።**

**ይህን ቅጽ በመፈረም ምን ዓይነት ፈቃድ እየሰጠሁ ነው?**

የ SSI ክፍያዎችን ለመቀበል ብቁ ሆኜ ከተገኘሁ፣ የኔን ከኋላ የቀሩ የተፈጸሙልኝ የSSI ክፍያዎችን፣ ማለትም እኔ ከማገኘው የሕዝብ ድጋፍ መስጫ ገንዘብ መጠን ጋር እኩል የሆነ ገንዘብ የSSA ኮሚሽነር ለስቴቱ እንዲከፍለው በስሜ ጥያቄ እንዲያቀርብ ፈቃድ እየሰጠሁት እንደሆነ ተረድቼያለሁ።

**ስቴቱ ይህን ፈቃድ መስጫ እንድፈርም ለመጠየቅ ሕጋዊ ስልጣን አለው?**

አዎ። በሕግ አንቀጾች WAC 388-400-0060 እና RCW 74.62.030 መሰረት በስቴት የሚሸፈን የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለመሆን ይህን ፈቃድ መስጫ መፈረም አንዱ መስፈርት ነው። ይህን ፈቃድ መስጫ አልፈርምም ካልኩ፣ የስቴት የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ ማግኘት አልችልም።

**SSA ሙሉውን ከኋላ የቀረ ክፍያ ለእኔ ቢልክልኝ ምን አደርጋለሁ?**

ለተመሳሳይ ጊዜ የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ የ SSI ጥቅማጥቅሞች ማግኘት እንደማልችል ተረድቼያለሁ። SSI እንዳገኝ ፈቃድ ሳገኝ፣ የማገኘው የስቴት የሕዝብ ድጋፍ ገንዘብ ዕዳዬ እንደሆነ እና መልሼ መክፈል እንዳለብኝ ተረድቼያለሁ። ለስቴቱ መልሶ ሳይከፈሉ የቀሩ SSI ከኋላ የቀሩ ክፍያዎች ከተቀበልኩ፣ የፋይናንስ ገንዘብ ማስመለሻ ቢሮ (Office of Financial Recovery) በስልክ ቁጥር 1-800-562-6114 ደውዬ በማሳወቅ ዕዳውን እንዴት መልሼ መክፈል እንዳለብኝ የሚሰጡኝን መመሪያ እከተላለሁ።

**ፈቃድ መስጫው ለምን ያህል ጊዜ በሥራ ላይ ይቆያል?**

ፈቃድ መስጫው ተቀባይነት እንዲኖረው በእኔ እና በስቴት ተወካዩ መፈረም አለበት። ስቴቱ ከተቀበለው ቀን ጀምሮ ለአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት በስቴቱ እና በእኔ ላይ ገዢ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በዛን ጊዜ ለSSI ፋይል ለማስገባት ስምምነቴን እገልጻለሁ።

አንድ SSI ማመልከቻ **ሲቀርብ፣** ይህ ፈቃድ መስጫ **የጸና ሆኖ የሚቀጥለው** እስከ፥

- የመጀመሪያ SSI ክፍያዬን እቀበላለሁ፣ ወይም
- እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ወይም አስተዳዳራዊ የይግባኝ ጥያቄ ፋይል አላቀርብም እንዲሁም ፋይሉ በሥራ ላይ እንዲቆይ የተፈቀደው ከፍተኛው የጊዜ መጠን ላይ ደርሷል፣ ወይም
- ስቴቱ እና እኔ ይህን ፈቃድ መስጫ ለማቋረጥ ተስማምተናል።

**ስቴቱ ለ SSA ይህን ፈቃድ መስጫ በፈረምኩ በ ቀናት ውስጥ ካላሳወቀ ይህ የፈቃድ መስጫ ግዴታዎች እና ደንቦች በኔ ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።**

**ይህ ፈቃድ መስጫ ለ SSI ጥቅማጥቅሞች ጥበቃ ለማግኘት ፋይል እንደማስገባት ይቆጠራል?**

አዎ፣ ከዚህ ቀደም SSI ማመልከቻ ያላስገቡ ከሆነ፣ SSA ይህን ቅጽ መቀበል እና ይህን ፈቃድ መስጫ የፈረምኩበትን ቀን ለSSI ፋይል እንዳስገባሁበት ቀን አድርጎ እኔ SSI ማመልከቻ አስገብቼ ከሆነ ፈቃድ መስጫውን ከፈረምኩበት ቀን በ60 ቀናት ውስጥ እንደተቀበለው አድርጎ የመቁጠር ግዴታ አለበት። በ 60 ቀናት ውስጥ ለ SSI ጥቅማጥቅሞች ማመልከቻ ሳላስገባ ብቀር፣ ይህ ፈቃድ መስጫ ለ SSI ጥበቃ ለማግኘት ፋይል እንዳስገባሁበት ቀን ሆኖ አያገለግልም።

**ይህን ፈቃድ መስጫ በተመለከተ ስቴቱ በሚወስደው እርምጃ የማልስማማበት ነገር ካለ አስተዳዳራዊ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለኝ።**

| የደንበኛው ፊርማ | ቀን |
|---|---|
| DSHS ተወካይ ፊርማ | DSHS የተቀበለበት ቀን |



Barcode label

18235